# አንች ከንቱ የእንጀራ-እናት ወይስ እኛ ክፉ የእንጀራ-ልጆች?

*በላይነህ አባተ* ([abatebelai@yahoo.com](mailto:abatebelai@yahoo.com))

ከናንተ ባላውቅም የእንጀራ ትርጉም በቧለሙያ ወይዘሮ ሸው ተደርጎ ተዞሮ በሰታቱ ምጣድ ተጋግሮ አይናማ ሆኖ ከሚወጣ ህብስት ሰፋ ያለ ነው። ለእንጀራ ብዬ አገለገልኩ፤ ለእንጀራ ብዬ ተሰደድኩ እንዲሉ። አዎ ወደንም ሆነ ተገፍተን እንጀራ እንኳን ታይቶ ቃሉ ተሰምቶ ወደማይታውቅበት ቦታ የምንነጉደው ሳይቀር ለመኖር ስንል፤ ለእንጀራ ስንል ተሰደድን የምንል አለን። እንግዲህ እንጀራ ከሆድ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመኖር፣ ከህልውና ወዘተርፈ ጋር የተቆራኘ ነው ማለት ነው።

የእንጀራ እናት እንደዚሁ እንጀራ የምትሰጥ፣ እንጀራ ብቻ የምታቀርብ ሳትሆን ቂጣውንም፣ ጨጨብሳውንም፣ አንባሻውንም፣ ቆጮውን እንኳን ሌላ፣ ሐምበርገሩን፣ ፓስታና መከሮኒውን የምትሰጠውም እናት ናት። እንደሚታወቀው የእንጀራ እናትና የእናት ልዩነት የሚያተኩረው በመጀመሪያ ዘጠኝ ወር አርግዛ፣ አምጣ አለመውለዷ ላይ ከዚያም በእናትና በልጅ መካከል ያለው የጠበቀው ተፈጥሯዊ መንፈሳዊ ትስስር አለመኖሩ ላይ ነው። ዳሩ ግን ወላጅ እናትን የሚልቁ የእንጀራ እናቶች  ወይም ተምጠው የተወለዱትን ልጆች እጅግ የሚያስንቁ የእንጀራ ልጆች መኖራቸው አይካድም። መቸስ የዚህ አለም ነገር አስቸጋሪ አይደለም! የጻድቃንን ያህል ባህሪ ያላቸው የእንጀራ እናቶች  ወይም ልጆች ቢገጥሙን እንኳን እንደ እናት ወይም ደሞ እንደ ልጅ ለማየት አቅቶን ትዝብት ላይ የምንወድቅ ሰዎችም አንታጣም። በኔ አመለካከት ትናንትም ሆነ ዛሬ አንዳንድ በቃኝን የማያውቁ አረመኔ ልጆቿ እንደ መዥገር ከጀርባዋ ላይ ተጣብቀው አንወርድም እያሉ ወተቷንም ደሟንም በባቄላ አገዳ በመምጠጥ ልጆቿን ቀልባ የማታድር ችጋራምና ንፉግ ያስመስሏታል እንጅ ጦቢያ ለእናትነት የሚያንስ ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ሐብት ኖሯት አያውቅም። እጣ ፈንታዋ ሆኖ የጦቢያ እጇ አመድ አፋሽ ነው። እርሷ ገላዋ በሸቀን ተወርሶ እያለ ወደ ዉጪ ሳይቀር ልካ አስተምራ እናትነቷን እንክዳታለን። አምጣ ወልዳ አሳድጋን የወጣንበትን ማእጸን እየቀደድን የወንበር መቀመጫ ድብዳብ ወይም የከርስ መሞያ ቋንጣ እናደርገዋለን።

የእንጀራ እናት በሴትና በልጅ መካካል ያለ ግንኙነት ነው። ሴት የእንጀራ እናት ከሆነች ከሌላ ሴት ልጆች የወለደ ወንድ አግብታለች ማለት ነው። ልጅም የእንጀራ ልጅ ከሆነ አባቱ ከናቱ ውጭ ሌላ ሴት አግብቷል ማለት ነው። ማን እንደጀመረው ባላውቅም ጦቢያ ሁሌ በሴት ትመሰላለች። ጦቢያ ረጅም እድሜ እንዳላት፣ በዚህ ረጅም እድሜዋም በርካታ ልጆችን እንዳፈራች፣ እንደማንኛውም ሴት ደግሞ ስትጸንስ፣ ስታረግዝ፣ ስትወልድ ወይም ሲያስወርዳት፤ ልጅ ስታሳድግ ወይም ሲሞትባት፤ ለቁም ነገር ስታደርስ አለዚያም ቀረ-በከንቱ ሆኖ ሲቀርባት መኖሩን በሚገባ የምናውቅ ይመስለኛል። ከጥንት ጀምሮ  ወራሪ ከሩቅም ከቅርብም እየመጣ በሯን መሰስ ብሎ እየከፈተ መቀነቷን ሊያስፈታት፣ ቀሚሷንም ሊያስወልቃት ሲቃጣ፤ ብዙዎቹ ቆፍጣና ልጆቿ ህይወታቸውን ሰውተው የክብር ቀሚሷን ሸሙንሙን አድርጋ ለብሳ፣ የጥበብ መቀነቷን ጠበቅ አድርጋ ታጥቃ ለአያሌ ክፍለ-ዘመናት እንድትኖር ማድረግ መቻላቸውን እንኳን እኛ አለም በሙሉ የሚያውቀው ጉዳይ ይመስለኛል። ይህችን ወይዘሪት እንደ ክፉ እንጀራ እናት እያዩ ግፍ ለመፈጸም የሚመጡትን ባእዳን እየመሩ ያመጡ፤ ዛሬ አፈር ሆኖ ለቀረው ጨጓራቸው ሲሉ ያስለቀሷት ልጆችም ነበሯት።

ለእርሷ እንዳለመታደል፣ ለእኛም እንደመረገም ሆኖ ጦቢያ እንኳን በሯ ግርግዳዋ ዙሪያውን ፈራርሶ፤ መቀናቷ በመተርተር ላይ፣ ቀሚሷም በመውለቅ ላይ ያለው ዛሬ፣ አሁን በኛ ጊዜ ነው። ሲያሳፍር!! እንዲያውም የክብር ልብሷ ከመገፈፍ አልፎ ያ የምናውቀው መቃ አንገቷ በሐሰትና በድንቁርና ምሳር ተቆርጦ ተጥሏል። በዚያም አላቆመም ፍሪንባዋ፣ ሸንጡዋና መቀመጨዋና ሌላውም አካልዋ በክህደት ቢላዋ እየተመተረ በመቅቡጥ መልክ በመሰጠት ላይ ይገኛል። በአቀንጣጤ ጥርሱ የሚግጥን አውሬ በካራ እየዘለዘለ የሚያግዝ እንጅ ከአውሬ የሚከላከል ልጅ ጦቢያ ዛሬ እጅግ ያጠራት ይመስላል። ዛሬ ዛሬ ልጆችዋ ከአንጋታችን በታች ጉች ጉች ብሎ ከተቀመጠው ሆዳችን ባሻገር ማየት ተስኖናል። ነቢዩ ሐዲስ አለማየሁ በየእልም-ዣት መጽሐፋቸው እንደተነበዩት ጦቢያን እስከ ወዲያው ልንክዳት ዳርዳር ብለናል። እንዲያውም ሙጥጥ አድርገን አይናችንን በጨው ታጥበን የካድናትም ስንክ ሳር ሆነናል። እንዲያው ምን አይነት አይነ-ጥላ ሰፈረብን ይሆን? ባል አግብታ ሳታውቅ እርሷ ክፉ የእንጀራ እናት ሆነችና አረፈችው ወይስ ልጆችዋ በምናብ ወደ አረመኔ የእንጀራ-ልጅነት ተቀይረን ቁጭ አልን?

ትርጉሙ እንደሚነግረን የእንጀራ እናት ለመሆን መጀመሪያ ባል ያስፈልጋል። አቶ ባልም  ከሌላ ሴት የወለደው ልጅ መኖር አለበት። ጦቢያ ግን እንኳን ባል የከንፈር ወዳጅም አላት ሲባል ሰምቼ አላውቅም። ልብ ብሎ የሚያነብ አንባቢ ወንድ ከሌለ ልጆችዋ እንዴት ተወለዱ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ታሪክ ወይም ሌላ ነገር ተመራማሪዎች ባለቤቷ እገሌ ነበር ብለው በቂ መረጃ እስካላመጡ ድረስ መልሱ “ጦቢያ ልጆችዋን የወለደቻቸው በድንግልና ነው” የሚል ነው። አዎ ጦቢያ ድንግል እንደሆነች ታሪኳ ይመስክራል። ማርያም በድንግልና አንድ ልጅ ወልዳ እርሱም ተባርኮላት የአለም መድሐኒት

ሆኗል። እንደ ቅድስት ማርያም ከትልቁ መጣፍ ላይ የዋለችው ጦቢያ በበኩሏ በርካታ ልጆችን ወልዳለች። ዳሩ ግን ወልዳ ያሳደገችን ሁሉም አልተባረክንላትም። ታሪክ እንደሚነግረው አያሌ ልጆቿ ተሰውተው ክብሯዋን ጠብቀዋል። ለተቀረው አፍሪካ እንደዚሁም ለሌሎች በባርነት ሰንሰለት ተቀፍድደው ለሚኖሩ ሕዝቦች አርአያና መድህን ሆነዋል። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ ሌሎቻችን ግን ወደ አሳፋሪ፣ አዋራጅና ከሰው በታች ወደ እሚያውል አሽከርነትና ሎሌነት ተቀይረን በባርነት ቀንበር ሲማቀቁ ከኖሩት እናቶችም በታች አስቀምጠናታል። አዎ በተለይ አሁን አሁን ብዞዎቻችን ናቅናት፣ ሰደብናት፣ ይሉኝታ ቢስ ሆንባት፣ በድብቅም ባደባባይም ሸጥናት። ይህም ብቻ አይደለም በመጥረቢያ እየከተከትን የድሮ መልኳንና ቁንጅናዋን ከማጥፋት ባሻገር፣ ጉረሮዋን አንቀን እንስተንፋሿን በመዝጋት በጣረሞት ላይ እያለች ከአልጋ ላይ አውርደን ወለል ላይ አስተኝተን ደቀደቅናት። የለንበትም እያልን ወይም ደሞ ሌላ ሌላ ሰበብ እየፈጠርን ተደብቀን መጠጡን መብሉን እንደ እንሰሳ እየበላንና እየጠጣን የምንኖርም ብዙ የምንሻል አይመስለኝም። እንኳን እናቱ የእንጀራ እናቱ ወይም እንዲሁ የማያውቋት ስውስ ብትሆን በአረመኔ መቀስ አካሏ እየተቆረጠ ሲጣል ዝምብሎ የሚያይ ሰው ሰው ይባላልን? ቢያንስ ቢያንስ በደመ ነፍስ “የሰው ያለህ ድረሱላት!” ብሎ መጮህ አለ እኮ!

ያልተገራ ልጅ፣ አዋራጅ ልጅ፣ ክብርን የማያውቅ ልጅ እንኳን ለናቱ ለራሱም አይሆን። በዚህም የተነሳ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እርቋን በሰላ መቀስ እየቀረጠፍን ከማሳነስና መልክ ከማሳጣት አልፈን፤ በአንድ ጎጆ ውስጥ መወልዳችንን በመካድ፤ አንተ ወንድሜ አንችም እህቴ አይደለሽም እየተባባልን ተለያዬን። አንተም በሚናህ እኔም በሚናዬ እየተባባልን በቤተ-ክርስቲያን ሳይቀር ተዋህዶን አፈረስን። እኔ አውራ ካልሆንኩ እኔ ብቻ እንደ ልቤ ጮቤ ካልረገጥኩበት በረቱ ይናወጥ ወይም ይፍረስ እያልን እንሰሳውን ሁሉ ጤና ነሳን። “የኔን መርህ ካልተከትልክ ጠላቴ ነህ “ በሚል ከንቱ መንፈስ እየተበረዝን ወንድማማቾች፣ እትማማቾች ስንፋለጥ መዋሉን ተግተን ቀጠልን። የጋራ ጠላት ተቀምጦ እኛው እርስ በርሳችን እግራችንን አንቧትረን መዘረጣጠጡን ዛሬ በዚች ሰዓት እንኳን አላቆም አልን። ጉድ እኮ ነው! እርስ በራሳችን እንደ አይጥና ድመት ስንፈላለግ ጦቢያ በድንግልናዋ ቅድስት ሆና እንድትኖር ለማይፈልጉት ሐጆች (ለቃሉ ይቅርታ አመንዝራዎች) በሩን ቡኣ አርገን ከፍተን ሰጠን።

ቂም ይዘውባት የኖሩ ባእዳን እኛን ከንቱ ልጆቿን ስኳርና ጨው እያላሱ ይደፍሯት፤ እንደፈለጉ ያሽከረክሯት፣ እንደ ወንጭፍ እየወረወሩ የወፍ ማባረሪያ፣ የሰብላቸው መጠበቂያ ያደርጓት ጀመር። ልጆቿ ስኳር ወይም ጨው ላሽና የማይልስ ሆነው ተከፋፍለው እርስ በራሳቸው መተረማመሱን ቀጠሉ። ስኳር ቃሚው ግደሉ፣ እሰሩ፣ አሰቃዩ፣ ንብረት ግፈፉ ብሎ ቀጭን ትዛዝ ሰጪ፤ ጨው ላሹም ትእዛዝ ተቀባይ ተላላኪ፤ ሁለቱንም አልቀምስ ባፍንጫዬ ይውጣ ያለው ደግሞ ተገዳይ፣ ታሳሪ፣ ንብረት ተገፋፊ፣ ተሰዳጅ ሆነን አረፍነው። ስኳር ቃሚውንም ሆነ ስኳር አልቅምም ያለውን አንጠጋም ያልን ደሞ ሳር እንደሚግጥ እንሰሳ እየበላን እየጠጣን አድፍጠን ሞትን መጠባበቅ ቀጠልን። አዎ ሞት እንደሁ እንኳን እናትን በመክዳት አልጋ ስር ቢደበቁም አይቀር!! እውነቴን ነው! መኮነን መጽደቅህን ባላውቅም በጊዜአዊ መቅቡጥ አይንህ ተሰውሮ የወደፊቱን ትውልድ እጣ ፈንታ በማጨለም ላይ ያለህ ወይም ሲጨልም ዝም ብለህ እየተመለከትክ ያለህ ሁሉ መሞትህ አይቀርም!! አዎ ሞትን በጭራሽ አታመልጣትም፤ አንድ ቀን ትሞታለህ!!

ግፍ እንደ ዝናብ በሚዘንብባት ጦቢያ አንዱ ሬሳ ተረማምዶ ቤተ-ሰይጣን ገብቶ ሲፍነሸነሽ፤ ሌላው መንገድ ዳር ቆሞ ለማኝ ሆነና ቁጭ አለ። ጥቂቶቻችን በጉቦ፣ በሸር፣ በተንኮል ከብረን ስንናጥጥ ሌላው በጠኔ በበሽታ በእምቦቀቅላ እድሜው መቀጨቱን ቀጠለ። አንዱ ውሸቱን፣ ቅጥፈቱን፣ ተንኮሉንና ክፋቱን በሕዝብ መገናኛ መንገዶች እንደ ነሐሴ ጎርፍ አለገደብ ሌተቀን የመልቅቅ መብት ሲሰጠው ሌላው እውነትን እንኳን እንዳይናገር አንደበቱን መለጎሙ እየበረታ መጣ። ሕዝብ ላቡን አንጠፍጥፎ በሰራው የቤተ-መንግስት አዳራሽ ጥቂቱ እንደ ጉልቻ ተጎልቶ ሲውል ሌላው በጎልማሳና በሽምግልና እድሜው በሰፈር ዳስ ውስጥ እንኳን እንዳይሰበሰብ፤ እንዳይመካከር ተከልክሎ ሆነ ብሎ ቆሎ በጀላፉ እግሩ እንደደፋ ልጅ “ውጣ ከዚህ” እየተባለ እየተባረረ ፍዳውን መብላት ያዘ።

እርግጥ ነው ይህ ሁሉ ኢፍትሐዊነት የሚፈጸመው በአንዲት እናት በጦቢያ ጎጆ ውስጥ ነው። ግፍ ፈጻሚው የእናት ልጅ ግፍ ተቀባዮችም የእናት ልጆች ናቸው። ይህንን ሁሉ መከራ እየተቀበለች ስታለቅስና ስትደማ የምትኖረውም እናት ናት፡። የእንጀራ ልጅ ለእናት የማይመች ክፉ ቢሆን ብዙም ላይገርም ይችላል። አምጦ የወለዱት ልጅ የተፈጥሮ ሕግንም ሆነ የህብረተሰብን ደንብ ጥሶ የእንጀራ-ልጅ እንዲያውም ለነፍስ-የሚያሰጋ አረመኔ ፍጡር ሆኖ ሲገኝ በምን ቋንቋ ይገልጹታል? ለማንስ እግዚኦ ብሎ ብሶትን ይነግሯል? ትሰሚኛለሽ፤ ጦቢያ? እንኳን የግል ልጅ ያለው ባል የከንፈር ወዳጅ እንኳን ሳይኖርሽ ከትርጓሜ ውጪ በግድ አንቺ ለገዛ ልጆችሽ ከንቱ- የእንጀራ እናት ሆንሽና አረፍሽው ወይስ የወለድሽን ልጆች ቆራርጠው ወደ እሚጥሉ መርዘኛ የእንጀራ ልጆች ተቀይረን ቁጭ አለን?

ሐምሌ ሁለት ሺህ ዓ.ም.